## ዝምታየም ቤሆን የጌዜ ሚዛኔ፤ በሕሌናዬም ነው ማሰብ የሚገባኝ

ዝምታየ እኮነው የጌዜ ሚዛኔ
እንደ ትምሳሌነት እንደሚነገረው
"ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ"
አይደለሁም እኔ።
በሕሌናዬም ነው ማሰብ የሚገባኝ
ወንድሜ አዳምጠኝ፣
ፈጥነህ ሳትኮንነኝ፤
**አንተ የቁንቋው ሊቅ፣ ግዕዙን አሥረዳኝ።**
ትላንት ለሙብት ቆመህ
እስር ቤት ስትጓዝ
ያኔ የደገፍነህ ነበረ በአቋምህ
አንተ የቁንቋ መምህር
ዛሬ ምኑ ነካህ፣ እስኪ ልጠይቅህ፤
የጎሣ መስቀልህን
አንግበህ የታየህ።
**አንተ የቁንቋው ሊቅ ግዕዙን አሥረዳኝ**
ድንገት ካላነበብህ፤
እኔ ልጥቀሥልህ።
እንደትንቢት ሆኖ
ቀድሞ ከተጻፈው
ይገርማል ይደንቃል፤
ላንተም ጭምር ሆኗል።
ጥቁር መልክ ስላለህ ልትፍቀው አትችልም፤
ሌላው ሁሉ ቀርቶ በጎሣ ብታምንም።
ነብዩ ኢርምያስ ተነበየ እንዲዚህ፣
"በውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን
ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን
ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?
በዚያን ጊዜ ክፋትን
የለመዳችሁ እናንተ ደግሞ
በጎ ለማድረግ ትችላላችሁ።" - እርምያስ 13:23
ዝምታየ እኮነው የጌዜ ሚዛኔ፤
"ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ"
እንደሚባለውም አይደለሁም እኔ።
ወንድሜ አዳምጠኝ፣
ፈጥነህ ሳትኮንነኝ፤
በሕሌናዬም ነው ማሰብ የሚገባኝ።
ወጣቷ ሕሌና ጊዜውን በዋጀች፣
በተሰጣት ጸጋ ሁሉን ከሚሰጠው

ፈጣሪ እግዚአብሔር፤
ያልተጻፈን ማንበብ
ምነው መረጥህሳ
አንት የቋንቋ-የእንግሊዙ መምህር።
**እስኪ እንገምግም ጠልቀን ፤**
**ደግሞም እናማከር፣**
ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ "ስለመንጋ" ያሉትን።
ያስፈልጋልና ከፍ ያለ ጥንቃቄት
ስንትገረጉም ያን ቃል፤
እንዳይሆን አደራ
"ኃጢያተኛ ሳያሳዱት ይሸሻል።
አዛውንትም እንዲህ ብለዋል፣
"አትፍረድ ይፍረዱ፤
በቆፈሩት ጉድጓድ ሳይገቡም አይቀሩ።"
ይህን ይሰቡበት የእንግሊዙ መምህር፣
ጠበንጃ አይደለም የሕሌና ነገር፤
አጥንትን ሰባብሮ የሚዳርግ ለቀብር።
ትላንት ለሙብት ቆመህ
እስር ቤት ስትጓዝ
ያኔ የደገፍነህ ነበረ በአቋምህ
አንት የቋንቋ መምህር
ዛሬ ምኑ ነካህ፣ እስኪ ልጠይቅህ፤
የጎሣ መስቀልህን
አንግበህ የታየህ።

© ለምለም ፀጋው፤ September 29, 2019
Inspired by Helena Desalgen poem and, her critics

በዩትዩብ #ለመፃፍ #ነፃኢንተርኔት
Ethiopia: ህሊና መንጋ ያለችው ማንን ነው?? አርቲስት በሀይሉ ነቃዓጥበብ & ጦቢያ ግጥምን በጃዝ #88-11 ህሊና ደሳለኝ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የተላለፈ መልዕክት, **May 13, 2019**